የቡረጋርድ ዕቅድ፣ የማሕበረሰቡን የወደፊት ኑሮ መቅረጽ

WWW.ALEXANDRIAVA.GOV/BEAUREGARDPLAN

ነዋሪዎች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ ማሕበራዊ ድርጅቶች፣ በአቅራቢያው ያሉ ሲቪክ ቡድኖች እና ባለንብረቶች በቀጣይ 20 እና 30 አመታት በቡረጋርድ አካባቢ ሊታይ የሚችለውን የእድገት ራዕይ ለመፍጠር ከከተማው ጋር ከአንድ አመት በላይ ሲሰሩ ቆይተዋል። ይህ የማህበረሰቡ ራእይ የቀረበውን ዕቅድ በማዘጋጀቱ ላይ ውሏል።

ዕቅዱ (ፕላኑ) ምንን ያስፈጽማል፤

በሰዎችና በሚያዘወትሩዋቸው ቦታዎች መካከል አመቺ መገናኛ መንገዶችን መፍጠር፤ ነዋሪዎች ፈጣን ወደ ሆነው የትራንስፖርት ጣቢያ፣ አዳዲስ የምግብ ሸቀጣሸቀጥ ሱቆች፣ ፓርኮችና ፕላዛዎች፣ የቢሮ ሕንጻዎች፣ እና ብዙ የሸቀጣሸቀጥ ቦታዎች በሰባት ደቂቃ ወይም ባነሰ ጊዜ በእግር ይደርሳሉ። በቡረጋርድና ሳንገር መንዶች መገናኛ የሚሰራ አዲስ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ ፈጣን የድንገተኛ አደጋ ምላሽ በመስጠት የተሻለ የሕዝብ ደህንነት ለከተማው ምዕራባዊው ጫፍ ይሰጣል።



የአካባቢው ትራፊክ (ተሽከርካሪ መዟዟር) ማሻሻልና የትራፊክ መጨናነቅን መቀነስ። በቡረጋርድ አካባቢ የመንገዶች መሻሻልና ተጨማሪ መተላለፊያ መንገዶች መኖር የትራፊክ መጨናነቅን ይቀንሳል። ሰፋ ያሉ የእግረኛ መንገዶችና መሻገሪያዎች ለእግረኞችና ለብስክሌት ተጠቃሚዎች ምቹ አገልግሎት ይሰጣሉ፤ ለተወሰነ አገልግሎት የተመደቡ የመንገድ መስመሮች (ለይንስ) አስተማማኝና ብቃት ያለው የመተላለፍ አገልግሎት ይፈጥራሉ። በመጓጓዣ መሻሻል፣ በተጨማሪ መኖሪያ ቦታዎች፣ ቢሮዎች፣ እና በሁሉን-አቀፍ እድገት ምክንያት ቡረጋርድ አዲስ የተለየች ስፍራ ትሆናለች።

ደዲከትድ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶች መፍጠር፤ በጸደቀው የቡረጋርድ ፕላን መሰረት ያረጁ የአፓርትመንት ሕንጻዎችን በ30 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በአዳዲስ መቀየር፤ በግምት 700 የሚሆኑ የፈረሱ ቤቶች ተመጣጣኝ በሆኑ ኮሚትድ እና ዎርክፎርስ ሀውሲንግ ይተካሉ። በሽግግሩ ወቅትም የከተማው ቢሮ የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ከቦታ ለውጥ ጋር የተያያዘ ትርጉም ያለው አገልግሎትና እርዳታ እንዲያገኙ ከአልሚዎች ጋር ይሰራል።

በከተማና በተፈጥሮአዊ አከባቢዎች ቀጣይነት ያለው ሽግግር መፍጠር። አብዛኛዎቹ አዳዲስ ቤቶች ከአከባቢው መናፈሻዎች ወይም አዳዲስ ክፍት ቦታዎች ከእሩብ ማይል በማይበልጥ ርቀት ውስጥ ይሆናሉ። ማህበረሰቡ እቤቱ አጠገብ እየተሰባሰበ የአካል እንቅስቃሴ ለማድረግ፣ ስፖርት ለመጫወት፣ እንዲሁም እውጭ ለመዝናናት አዲሱ የአትሌቲክስ ሜዳ፣ የእግረኛ መንገዶች፣ መንሸራሸሪያ መንገዶች እና የብስክሌት መንገዶች ግንኙነት ሆነው ያገለግላሉ። አዲሶቹ ቤቶች ኤነርጂ (ሃይል) ቆጣቢና ለአከባቢው ተስማሚ ሆነው የሚሰሩ ይሆናሉ።

በሚጸድቀው ዕቅድ መሰረት የቡረጋርድ ግንባታ እነዚህን ያካትታል።

ማህበራዊ መሻሻልን ማዕከል ያደረገ ግንባታ ማድረግ

የገበያ ቦታዎች፣ ቢሮዎች፣ ሆቴል፣ እና መኖሪያ ቤቶች እርስ በርስ የተገናኙና በተቀናጀ መልኩ በህዝብ ትራንስፖርት መስጫ ጣቢያዎች አከባቢ የሚሰሩ ይሆናሉ።

ብዙ የምግብ ቤት ምርጫዎች፣ አዲስ የምግብ ሽቀጣሽቀጥ መደብር፣ እና አሁን ያሉትን የምግብ ሽቀጣሽቀጥ መደብሮች የሚያስፋፉ የሰፈሩ የገበያ ቦታ ያለው

ከ700 በላይ አዳዲስ ደዲከትድና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ተሰርተው አሁን ካሉት ውስጥ 28% መኖሪያ ቤቶቹን ይተካሉ።

ለሰፈሩ የተሻለ ፈጣን የምላሽ ጊዜ የሚኖረው አዲስ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ

በሰሚናሪ መንገድና በቡረጋርድ መንገድ መገናኛ ላይ የተሻሻለ መተላለፊያ

ከግንባታው ጋር የተቆራኘ ፈጣንና ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት

አዳዲስ የወስጥ ለውስጥ መንገዶችና የእግረኛ መሄጃ በመስራት ትራፊኩን ማከፋፈል

የበለጠ ክፍት ቦታና ለማህበረሰቡ መዝናኛ የአትሌቲክስ ሜዳ

ወደ ትምህርት ቤቶች የሚያስከዱ የተሻለ እይታ ያላቸው የእግረኛ መንገዶች

የቡረጋርድ ዕቅድ ካልጸደቀ ምን ይሆናል?

ባለው ህግ መሰረት ግንባታው ወደፊት ይሰራል፣ ይሁን እንጂ ማህበረሰቡ በግል ለሚሸፈኑት የትራንስፖርት ማሻሻያዎች፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶች፣ ማህበራዊ ደህንነት፣ የሽቀጣ ሽቀጥ መደብሮችና መናፈሻዎች ማሰሪያ ከ148 ሚሊዮን ዶላር በላይ ያጣል።

ግንባታው በተቀናጀ መንገድ ሳይሆን በዘፈቀደ የሚሰራ ይሆናል።

አሁን ያሉት ክፍት ቦታዎች፣ መናፈሻዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ እና ሰፈሮች የታቀደላቸውን የእርስበርስ ማገናኛዎችን ያጣሉ።

አዳዲስ የሽቀጣሽቀጥ መደብሮችና ምግብ ቤቶች ለመኖራቸው ዋስትና የለም።

አዳዲስ የከተማ ቤቶችና ኮንዶሚኒየሞች ተመጣጣኝ ዋጋና የደዲከትድ መኖሪያ ቤትነት ዋስትና አይኖራቸውም።

ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት ወይም ከዛ በላይ አዲስ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ ስለማይኖር በማህበራዊ ደህንነት ላይ ተጨማሪ ጫና ይፈጥራል።

የተጨናነቀ ትራፊክና ደካማ የአውቶቡስ አገልግሎት ይኖራል።

የትራንስፖርት ማሻሻያው ከግንባታው ጋር ካልተቀናጀ የሰፈሩ አገልግሎት በየግል አካሄድ ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

አዳዲስ መናፈሻዎች ወይም ክፍት ቦታዎች አይኖሩም፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ዛፍ ይጠፋል።



የቡረጋርድ ‘ስሞል ኤሪያ ፕላን’ (መለስተኛ የአከባቢ ዕቅድ) የመጀመሪያ ረቂቅ ሃሳብ እንዲሰጥበት በኢንተርነት ወይም በሲቲ ሆል ቁጥር 1900 ክፍል፣ በበርክ ቤተመጻሕፍትና በቢትሊይ ቤተመጻሕፍት ገዝጇ ሆኗል። ከተማውና ማህበረሰቡ ዕቅዱን ለማሻሻል በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ የሕዝቡም አስተያየት ቢጨመር ይበረታታል።

WWW.ALEXANDRIAVA.GOV/BEAUREGARDPLAN